ማኅበራዊ ጥናት መድረክ
Forum for Social Studies

ታህሣሥ 1998 ዓ.ም.

# የፖሊሲ ፍሬ ሀሳቦች

ቁጥር 3

## የተበላለጠ የመሬት ግብር ሥርዓት አስፈላጊነት በኢትዮጵያ

- የማኅበራዊ ጥናት መድረክ በሀገሪቱ የልማት ችግሮች ዙሪያ ፖሊሲ-ነክ ምርምሮችን የሚያደርግ ለትርፍ ያልተቋቋመና መንግስታዊ ያልሆነ አገር በቀል ድርጅት ነው፡፡
- የምርምር ውጤቶቹን ለፖሊሲ አውጪዎችና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሱ ያደርጋል፤ ሕዝባዊ ውይይቶችን ያዘጋጃል፤ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ጋብዞ ያወያያል፡፡
- በአዲስ አበባ (97.1) እና በአዋሳ (100.9) ከተሞች ኤፍ.ኤም. ራዲዮ ጣቢያዎች ልማት ነክ ጉዳዮችን እያዘጋጀ ያሰራጫል፡፡
- በድረ-ገጹ በልማት ዙሪያ ውይይቶችን እያካሄደ ይገኛል፡፡ በአሁኑ ወቅት ለመወያያ የቀረበው ርዕስ *የምግብ ዋስትናን በኢትዮጵያ ማረጋገጥ ይቻላል?* የሚል ነው፡፡
- በርዕሱ ዙሪያ ሐሳብ መሰንዘር የምትፈልጉ በኢሜይል አድራሻችን ላኩልን፡፡

### 1. መግቢያ

ኢትዮጵያ በአለም ካሉ የአፈር እና ደን ሀብታቸው በእጅጉ ከተመናመነባቸው ሀገራት ቀዳሚውን ስፍራ ትይዛለች፡፡ በተለያዩ መንስዔዎች ሳቢያ በየአመቱ እስከ 200,000 ሄክታር ደን ይወድማል፤ ከእያንዳንዱ ሄክታር የእርሻ መሬት ደግሞ በአማካይ በያመቱ 42 ቶን የላይኛው ለም አፈር ይከላል (ይታጠባል)፡፡ ከፍተኛ ተዳፋትነት ባላቸው አካባቢዎች ደግሞ አሃዙ ወደ 400 ቶን ያሻቅባል፡፡

*ከሰላሳ አመታት በፊት በተካሄደ ሰፊ ጥናት ወደ ግማሽ የሚጠጋው የሀገሪቱ ኮረብታማ አካባቢ አፈር በመካከለኛና ከፍተኛ የክለት ደረጃ ይገኝ ነበር፡፡ ከዚያ ጊዜ ወዲህ የሕዝቡ ቁጥር በ 65% ሲያሻቅብ በተጓዳኙ ሊከሰት የሚችለውን የተባባሰ የአፈር መጎዳት ለመገመት አያዳግትም፡፡*

እንዲያውም ሥር እየሰደደ የመጣው የምርታማነት ማሽቆልቆል፤ ለድርቅ ተጋላጭነት፤ የቤተሰብ ምጣኔ ሀብት መዳሸቅ፤ ወዘተ... ተጨባጭ አመላካቾች ናቸው፡፡



ምስል 1. የእርሻ መሬቶች ያለማቋረጥ ማዕድናቸው ስለሚሟጠጥ ምርታማነታቸው በፍጥነት ያሽቆለቁላል (ሰሜን ሸዋ አካባቢ)፡፡

ይህን ችግር ለመፍታት የጉዳዩ ባለቤቶች ላለፉት ሰላሳ እና አርባ አመታት ከፍተኛ ርብርብ ሲያካሂዱ መቆየታቸው አይዘነጋም፡፡

1. ገበሬዎች፡- የችግሩ ግምባር ቀደም ተጎጂ በመሆናቸው የተለያዩ ድንቅ እና ባህላዊ የተፈጥሮ ሃብት አጠባበቅ እና አያያዝ ስልቶች የነበሯቸዋው ቢሆንም ከፊሎቹ ዘዴዎቻቸው በመሬት ጥበት ሳቢያ፤ ከፊሎቹ ደግሞ ‘ዘመናዊ’ በተባሉ፤ ነገር ግን የአካባቢ ሁኔታን ባላገናዘቡ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች በመተካታቸው፤ እየገዘፈ የመጣውን የአካባቢ መራቆት ሂደት ሊገቱት አልቻሉም፡፡
2. መንግሥት፡- በዘውዳዊው፤ በደርግም ሆነ በአሁኑ መንግሥት የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት ክብካቤ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፡፡ በርካታ ፖሊሲዎች፤ መርሃ ግብሮች እና ስልቶችም ተነድፈዋል፡፡ በተለይም በደርግ ዘመን ምንም እንኳን የገበሬውን ፍላጎትና የአካባቢ ሁኔታን ባላገናዘበ መልኩ በዘመቻና በግዳጅ መልክ በሰፊው የተካሄደ ቢሆንም ዘመናዊ እርከኖች፤ የደን ተከላዎች፤ ወዘተ... ተካሂደው የተወሰኑ ተስፋ ሰጪ ውጤቶች ተገኝተው ነበር፡፡ ሆኖም ግን በመንግስት ለውጥ ወቅት በተፈጠረው አለመረጋጋት አብዛኞቹ ስኬቶች ተቀልብሰው እንዲያውም የተባባሱ ችግሮች ተከስተዋል፡፡
3. መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (መያዶች)፡- ገበሬውን ባሳተፈ መልኩ የተፈጥሮ ሀብትን ለመንከባበከብ የሚያስችል ስልት ነድፈው ቢንቀሳቀሱም የስርጭት አድማሳቸው ከሀገሪቱ የቆዳ ስፋትና ከችግሩ ጥልቀት አንፃር ሲታይ ኢምንት ነው፡፡ እንዲያውም እንቅስቃሴው በምግብ ለስራ ድጎማ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በአብዛኞቹ ስፍራዎች የፕሮጀክቶቹ የሥራ ዘመን ሲያበቃ የገበሬው ተሣትፎም ተያይዞ እንደሚከስም ታይቷል፡፡
4. ተመራማሪዎች፡- የተፈጥሮ ሀብት ገጽታን፤ መራቆትን እና ክብካቤን በተመለከተ በርካታ ተመራማሪዎች ጥናቶቻቸውን በተለያዩ ሥነ-ምህዳሮችና የችግር አይነቶች ለይተው በማካሄዳቸው በሀገሪቱ በቂ ሊባል የሚችል መረጃ አለ፡፡ ነገር ግን አብዛኞቹ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እና የመፍትሄ ሐሳቦች በስራ ላይ ባለመዋላቸው ችግሩን ማስወገድ አልቻሉም፡፡

*የጉዳዩ ባለቤቶች ብዙ ጊዜያቸውን፣ ጉልበታቸውን እና ገንዘባቸውን ቢያፈሱም የአፈርም ሆነ የደን ሀብት መራቆቱ በመቀነስ ፈንታ እንዲያውም አድማሱን ማስፋቱን የቅርብ ጥናቶች ይጠቁማሉ።*

እየገዘፈ የመጣውን የአካባቢ መራቆት ችግር ለዘለቄታው ለመፍታት የሚቀርቡት ተደጋጋሚ መፍትሔዎች የመሬት ይዞታን በማሻሻል ወይንም በመቀየር ላይ ያተኮሩ ናቸው። በአንጻሩ ደግሞ በሀገሪቱ ያለው የመሬት ሥሪት መሬትን በመንግሥትና በሕዝብ ባለቤትነት የሚወስን ነው። መንግሥትም የመሬትን ጉዳይ ለድርድር የማይቀርብ የሞተ ጉዳይ ነው በማለቱ በጉዳዩ ላይ ተጨማሪ ውይይት ለማካሄድ ጊዜን እና ሀብትን ማባከኑ ፍሬ አልባ ነው የሚሆነው።

*የመፍትሄ ኃሳቦች አሁን በሥራ ላይ ያለውን የመሬት ሥሪት ታሳቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል።*

እርግጥ ነው የመሬት ሥሪቱ የገበሬውን የባለቤትነት ስሜትን ሙሉ በሙሉ የሚያሟላ አይደለም። ይህም የገበሬው የተፈጥሮ ሀብት ክብካቤ እንዳይጎለብት አንዱ ችግር መሆኑ አያከራክርም። ነገር ግን ብቸኛው ወሳኝ ጉዳይ ሆኖ ሌሎች አማራጮችን ሊጋርድ አይገባውም።

*ለምሳሌ በቅርቡ የወጣው የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ (ቁጥር 456/1997) ብዙ ያስወገዳቸው ማነቆዎች አሉ።*

ከመሬት ሥሪቱ ተፅእኖ ባሻገር ሌሎች በርካታ ጋሬጣዎች አሉ። ለምሳሌ የማበረታቻ ሚና፣ የግብር ተፅእኖ፣ የግንዛቤ ደረጃ፣ የቴክኖሎጂ አመቺነት፣ ወዘተ…። ስለዚህም በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ባለው የፖሊሲ ማዕቀፍ ውስጥ ሆኖ ሌሎች በርካታ ማነቆዎችን ለመፍታት መጣር ችግሩን በእጅጉ ለመቀነስ ይረዳል። ቀጥሎ ባሉት ንዑስ ክፍሎች በዚህ ጉዳይ የማጥመ ጥናት ያፈለቀው አማራጭና አዲስ የመፍትሄ ስልት ባጭሩ ይቀርባል።

## 2. ወደ አዲስ የመሬት ክብካቤ ማስከበሪያ ስልት?

*በኢትዮጵያ የአካባቢ ክብካቤን የተንተራሱ በርካታ ፖሊሲዎች፣ ስልቶችና መርሐግብሮች አሉ። ቢሆንም ብዙዎቹ በወረቀት ላይ ብቻ ሰፍረው የሚገኙ እንጂ በተግባር የማስፈፀም ብቃታቸው ውሱን ነው።*

በርካታ ታታሪ ገበሬዎች መሬታቸውን በአግባቡ ለመንከባከብ ቢጥሩም በጥቂት ደንታ ቢስ ገበሬዎች ድክመት ሣቢያ የተፈለገው ውጤት ሊገኝ እንዳልቻለ እሙን ነው። ነገር ግን በኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ ታታሪውን ገበሬ ለይቶ ሊያበረታታ የሚያስችል ሥርዓት አልነበረም፣ የለምም። እንዲያውም ታታሪም ሆነ ደካማ ገበሬዎች በተዛቡ ፖሊሲዎች ሳቢያ እኩል ሰለባ ነበሩ። ጥቂት ድጎማ ሲኖር እንኳ እኩል ተቋዳሽ በመሆናቸው ደካሞቹ ገበሬዎች እንዳይተጉ በእጅጉ አዘናግቷቸዋል። የመሬት ክብካቤ ደግሞ ብዙ ጉልበት፣ ገንዘብ እና የእርሻ መሬት የሚፈጅ ጉዳይ ነው። ለክብካቤው ብዙ ወጪ ከወጣ በኋላ እንኳ በአጭር አመታት ወጪውን አይተካም። በዚህም ሳቢያ ዘላቂነት ያለው የማበረታቻ ስልት አስፈላጊነት አያከራክርም።

የአካባቢ ክብካቤን ለማስከበር በርካታ ሀገራት የተለያዩ መፍትሄዎችን በተግባር አውለዋል። በተለይም እ.ኤ.አ 1991 በሪዮ ዲጄኔሮ (ብራዚል) በተካሄደው የተባበሩት መንግሥታት የአካባቢ ጉባኤ ላይ የጸደቀው "በካዩ ይክፈል" (*Polluter pays*) የሚለው መርህ በአለማችን ከፍተኛ ተቀባይነት አግኝቷል። በመርሁ መሰረት ውሃን፣ አፈርን፣ አየርን ወዘተ… ለብክለትና ውድመት የዳረገ ሁሉ በግንባር ቀደም ተጠያቂ ሆኖ ተጨማሪ ግብር እንዲከፍል ይገደዳል።

ግብር በየትም ሀገር ያለ እና የግድ መከፈል ያለበት የዜግነት ግዴታ ነው። ገቢውም የሀገር ኢኮኖሚን ለመደጎም ከመዋሉ ባሻገር በዜጎች መሃከል ሊኖር የሚችለውን የሀብት ልዩነትን ለማጥበብ ይረዳል። ስልታዊ በሆነ መልኩ ደግሞ ተፈላጊ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎችን በማጎልበት እና ያልተፈለጉትን ደግሞ በማዳከም ሚናውን ይጫወታል። ይህ በ ማጥመ የተከናወነ ጥናትም በአብይነት የሚጠይቀው "አሁን በስራ ላይ ያለውን የኢትዮጵያ የመሬት ግብር ሥርዓት ከገቢ ምንጭነት ባሻገር ለእርሻ መሬት ክብካቤ መደጎሚያና ማስፈፀሚያ ማዋል ይቻላል ወይ?" የሚል ነው።



ምስል 2. ቀድሞ ለእርሻ ይውሉ የነበሩ መሬቶች በመራቆታቸው ሳቢያ በፍጥነት ከምርታማነት እየወጡ ነው (መቂ አካባቢ)።

ይህ ጥናት "በካዩ ይክፈል" የሚለውን አለም አቀፍ መርህ በሀገራችን ካለው የመሬት መጎሳቆል ችግር ጋር በማጣጣም "መሬትን ያልተንከባከበ በእዳ ይጠየቅ" (ወይንም በሌላ አገላለፅ "መሬትን የተንከባከበ ይሸለም") የሚል መሰረተ ሀሳብ ለማጎልበት ይሞክራል።

በኢትዮጵያ ያለው አጠቃላይ የመሬት ግብር ክፍያ በሄክታር ብር 10.00 ሲሆን ለተጨማሪ ሄክታር መሬት ደግሞ ብር 7.50 ይከፈላል። ነገር ግን ተመኑ የመሬት ስፋትን ብቻ ታሳቢ ያደረገ ሆኖ የመሬቱን የማምረት አቅም አያገናዝብም። ይህ አሰራር ደግሞ በከባቢያዊ ጥበቃ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ይኖረዋል።

እየተስፋፋ ያለው የመሬት መራቆት አንዱ መንስኤ የገንዘብ እጥረት መሆኑን እና ለክብካቤ የሚያስፈልገውን ማበረታቻ በዘላቂነት ማቅረብ ዋናው ችግር ነው። ይህንን ችግር ስልታዊ በሆነ መልኩ ለመፍታት ደግሞ በየአመቱ በገበሬዎች የሚከፈለውን የመሬት ግብርን ከአካባቢ ክብካቤ ጋር ማጎዳኘት ብልህነት ነው። ይህም ጉድኘት

ወጥ (አሐዳዊ) ወዳልሆነ የመሬት ግብር ክፍያ ፅንሰ ሐሳብ ያደርሰናል፡፡

*ጥናቱ የተበላለጠ የመሬት ግብር ሥርዓት በመዘርጋት እየተባባሰ ያለውን የመሬት መራቆት ችግር ለመግታት አለማስቻሉን በተጨባጭ ለማሳየት ይሞክራል፡፡*

ይህም የሚሆነው ለታታሪ ገበሬዎች የግብር ማበረታቻ (ቅናሽ) በማድረግ ሲሆን መሬቶቻቸውን ለማይንከባከቡ ገበሬዎች ደግሞ ድጎማ አለማድረግ ወይንም ተጨማሪ የግብር መጠንን በመጫን ነው፡፡ ይህ አካሄድ ታታሪዎችን የበለጠ ሲያበረታታ በተቃራኒ ያሉትን ገበሬዎች ደግሞ በሂደት ወደ ተንከባካቢነት እንዲመጡ ይገፋፋል፡፡ ከዚህም በላይ ስልታዊ በሆነ መልኩ ለእርሻ ሥራ መዋል በማይገባው መሬት ላይ እየተካሄደ ያለውን ጎጂ የእርሻ መስፋፋትን ለመግታት ይረዳል፡፡

### 3. በመስክ ጥናት የተደገፈ መረጃ

የተበላለጠ የመሬት ግብር ሥርዓት ፅንሰ ሐሳብን በተግባር ለመመዘን በመካከለኛው የኢትዮጵያ ክፍል ለናሙና በተመረጡ ወረዳዎች በ1997 ዓ.ም በመስክ የተካሄደ ዳሰሳ ተደርጓል፡፡ በዚህም መሠረት ከአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን ሞጃና ወደራና የጣርማበር ወረዳዎች እንዲሁም በኦሮሚያ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን ግራር ጃርሶ ወረዳና የምስራቅ ሸዋ ዞን የዱግዳ ቦራ ወረዳ ተካተዋል፡፡ ለጥናት የተመረጡት ወረዳዎች በተለያየ የሥነ-ምህዳር ቀጣናዎች፣ በመሬት ሃብት ይዞታ፣ በተለያየ የመራቆት ደረጃ፣ በተለያየ የእርሻ አሰራር ደረጃ፣ በተለያየ የአፈር መከላት ደረጃ፣ ወዘተ… ላይ የሚገኙ በመሆናቸው አዲስ የቀረበውን የተበላለጠ የመሬት ግብር ሥርዓት ከተለያየ የአካባቢ ገፅታና ሁነቶች ለመመርመር ይረዳል፡፡

ከአራቱ ወረዳዎች 7 የገጠር ቀበሌዎች ተመርጠው በጥልቀት የተጠኑ ሲሆን የተለያዩ የገበሬ ቡድኖች (አዛውንቶች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች፣ የልማት ቡድኖች)፣ የልማት ጣቢያ ባለሙያዎች፣ የግብርናና የፋይናንስ ባለሙያዎች መረጃ በመስጠትና በውይይት ተሳትፈዋል፡፡

*ከቅኝቱ ለመረዳት እንደሚቻለው፡-*

- *የተፈጥሮ ሀብት መመናመን በተለያየ ደረጃ ላይ ቢገኝም አስጊ የሆነ የጋራ ችግራቸው ከመሆኑም ባሻገር በወደፊቱ የአካባቢ እጣ ፈንታ ላይ ገበሬዎቹ ጨለምተኛ አመለካከት እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡*
- *የመሬቶቻቸው ምርታማነት እያሽቆለቆለ በመምጣቱ ለተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ችግር ተጋላጭነታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡*
- *አፈርን ለመንከባከብና ለመጠበቅ የዘላቂ ድጋፍ (ማበረታቻ) እጥረት የጋራ ችግራቸው ነው፡፡*
- *ገበሬዎቹ ከአንድ በላይ የእርሻ ማሳ ያላቸው ናቸው፣ ይህም ባመዛኙ አንዱ ማሳ ጥሩ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ጥሩ ያልሆነ ሊሆን ስለሚችል የተለያየ የመሬት አጠቃቀም ስልት ለማጎልበት የሚያመቹ ናቸው፡፡*

ከዚህ ቀደም ይካሄዱ የነበሩ በርካታ የተፈጥሮ ሀብት ክብካቤዎች የነበሩ ቢሆንም ብዙዎቹ ከዚህ በታች በተጠቀሱት ምክንያቶች ሳቢያ የታለመላቸውን ግብ አልመቱም፡-

- እቅዶቹ ባመዛኙ ከላይ ወደታች የወረዱና ገበሬውን ያላሳተፉ ስለነበሩ፣
- እንቅስቃሴዎቹ በግዳጅና በዘመቻ የተከናወኑ በመሆናቸውና ሲተገበሩም የግለሰብ እርሻን ልዩ ገጽታ ያላገናዘቡ ስለነበሩ፣
- ዘላቂ የማበረታቻ መንገድ ባለመኖሩ፣ እንዲሁም
- የገበሬው ልማዳዊ ዘዴዎች ከግንዛቤ ባለመግባቱና ባለመጎልበቱ፣ ወዘተ

ጥቂቶቹ (በመያዶች የተከናወኑ) ክንውኖች ጥሩ ውጤት ያስመዘገቡ ቢሆንም ግድፈቶች ነበሩባቸው፡፡ ይኸውም ገበሬዎችን የእርዳታ ጥገኛ በማድረጋቸው የፕሮጀክቶቹ የስራ ዘመን ሲፈጸም ክብካቤውም አብሮ በመክሰሙ ነው፡፡

*ከጥናቱ ለመረዳት የሚቻለው በሀገሪቱ ያለው የመሬት ግብር ሥርዓት ወጥነት የለውም፡፡*

በአማራ ክልል የግብሩ ተመን በመሬት ስፋት መጠን ላይ ብቻ የተመረኮዘ ሲሆን በኦሮሚያ ክልል ግራር ጃርሶ ወረዳ ደግሞ ድሮ በነበረው በባለመሬቱ የሀብት ደረጃ ላይ የተመረኮዘ ነው፡፡ የግብር መጠኑ የተተመነውም ከበርካታ አመታት በፊት በመሆኑ በጊዜ ሂደት የመሬቱ መጠን ከፍ ወይም ዝቅ ያለ እና የቤተሰብ ገቢም በዚያው መጠን ልዩነት ሊያሳይ በመቻሉ አሁን አብዛኞቹ ገበሬዎች እየከፈሉ ያሉት ግብር ከያዙት የመሬት ስፋት ጋር ባብዛኛው ያልተጣጣመ ነው፡፡ የመሬት ግብር ሥርዓቱ በእርሻ መጠን ወይንም በሀብት ደረጃ ላይ ብቻ መታጠሩ ግድፈት እንዳለው ገበሬዎቹም ሆነ የእርሻ እና የፋይናንስ ባለሙያዎች ያምኑበታል፡፡ ሆኖም ግን ብዙዎቹ ገበሬዎች ሊታገሱት የሚችሉት ግድፈት ሆኖ ነው የተገኘው፡፡

የመሬት ግብር ማስተካከያ (እንደ ጥራቱ ደረጃ) ይደረግ ቢባል ብዙዎቹ ገበሬዎች ያሁኑ ይዞታችንን ልናጣ እንችላለን ብለው ስለሚሰጉ አሁን ባለበት መልኩ ከነግድፈቱ ቢቆይ ይሻሉ፡፡ ይህም የሆነው ከዚህ ቀደም በአማራ ክልል በተካሄደው የመሬት ሽግሽግና ድልድል ሳቢያ አንዳንድ ባለይዞታዎች መሬቶቻቸውን ማጣታቸውን በመመልከት ነው፡፡

*መሬቱን የሚንከባከብ ገበሬ እንዲበረታታ የመሬት ግብር ክፍያ መጠኑ ቢቀንስለት ገበሬዎቹ ደስተኛ እንደሚሆኑ ገልፀዋል፡፡*

ነገር ግን የመሬት ግብርን መክፈል በናሙና ገበሬዎቹ እይታ የዜግነት ግዴታ ብቻ ሳይሆን እግረ መንገዱንም የመሬት ይዞታ ዋስትና ማረጋገጫ ጭምር ተደርጎ እንደሚወሰድ ተስተውሏል፡፡

*"የላቀ ክብካቤ ላደረጉ ገበሬዎች ፍፁም የመሬት ግብር ስረዛ ቢደረግላቸውስ" ተብሎ የቀረበውን ሐሳብ ሁሉም ገበሬዎች ውድቅ አድርገውታል፡፡*

የገበሬዎቹ ፍላጎት ሌሎች ማትጊያዎች ቢኖሩ ወይንም እነርሱ የሚከፍሏቸው ሌሎች በርካታ መዋጮዎች ቢሰረዙላቸው ይመርጣሉ እንጂ በጥቂቱም ቢሆን የመሬት ግብርን መክፈሉ በመንግሥት መዝገብ ላይ ባለቤትነትን እንደማደስ ነው ብለው ያምናሉ፡፡ ገበሬና የመሬት ግብር መነጣጠል የለባቸውም የሚል ግንዛቤ አላቸው፡፡ መሬቶቻቸውን በአግባቡ በማይንከባከቡ ደግሞ የግብሩ መጠን ከፍ ቢልባቸው ሊኖር የሚችለውን ውጤት ተጠይቀው ሲመልሱ “ነገሩ እንግዳ በመሆኑ ለጊዜው ግለሰቡን ሊያበሳጨው ይችላል፤ ቢሆንም ቅሉ ጉዳዩ እየተለመደ ሲሄድ ግለሰቡ ጥቅምና ጉዳቱን በሒደት ተረድቶ ባህሪውን ሊያሻሽል ይችላል” ይላሉ፡፡

*በጥናቱ የተካተቱት ገበሬዎችና ባለሙያዎች የተበላለጠ የመሬት ግብር ክፍያ ሥርዓትን በመሰረቱ ተቀብለውታል ለማለት ያስደፍራል፡፡*



ምስል 3. ከፍተኛ ተዳፋትነት ያላቸው መሬቶች ያለምንም የአፈር መጠበቂያ ዘዴ ለእርሻ በመዋላቸው ለከፍተኛ የአፈር መራቆት እየተዳረጉ ነው (ወሎ፣ ባቲ አካባቢ)፡፡

ቀጣዩ ጥያቄ ደግሞ “ገበሬው በአግባቡ መሬቱን መንከባከብ ወይንም አለመንከባከቡን ማን ይበይንለት?” የሚለው ነው፡፡ ይህንን ብይን ለመስጠት በመጀመሪያ የእርሻ መሬት ምዘና መኖር አለበት፡፡ ይህም የእያንዳንዱን የእርሻ መሬት ተዳፋት መጠን፤ የአፈር ጥልቀት፤ የአፈር ክለት ደረጃ ታሳቢ በማድረግ ተስማሚውን የእርሻ ተክል አይነት (ጊዜያዊ/ቋሚ) እና አስፈላጊውን የአፈርና ውሃ ጥበቃ ዘዴ እዚያው በመስክ ላይ መወሰን ይኖርበታል፡፡ ከዚያም ብያኔውን እያንዳንዱ ገበሬ በየአመቱ መተግበር አለመተግበሩን በማመዛዘን ከሶስቱ አማራጮች በአንዱ ሊፈረጅ ይችላል፡-

1. በበቂ ሁኔታ የተገበረ ገበሬ - ማበረታቻ የሚገባው፤
2. በመጠኑ ብቻ የተገበረ ገበሬ - ማበረታቻ የማይገባው፤ እና እንደአስፈላጊነቱ ደግሞ
3. ተፃራሪውን የተገበረ-የግብር ጫና (ቅጣት) የሚገባው ናቸው፡፡

“የመሬቶቹን ምዘናም ሆነ የግብር ብያኔዎቹን ማን ይወስናቸው?” ተብሎ ለተጠየቀው ጥያቄ የተገኘው አጠቃላይ ምላሽ፡- ተግባሩ በቡድናዊ ስራ የሚከናወን ሆኖ የአባላቱ ስብጥርም ገበሬውን፤ የእርሻ እና የታክስ ባለሞያውን ማካተት እንዳለበት ነው፡፡

## 4. ማጠቃለያ

በሀገራችን የአካባቢን መራቆት ችግር ለመፍታት በርካታ ጥረቶች የተደረጉ ቢሆንም የተገኘው ውጤት እዚህ ግባ የማይባል ነው፡፡

*በርካታ የአካባቢ መጠበቂያ ቴክኖሎጂዎችና አጋዥ ፖሊሲዎች በበቂ ሁኔታ ቢኖሩም በተግባር ላይ የዋሉት በጣም ጥቂት ናቸው፡፡*

አንዱና ዋናው ምክንያት ክብካቤው ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅና ገበሬው ደግሞ ደሃ በመሆኑ ነው፡፡ የምግብ-ለስራ እና ሌሎች ማበረታቻዎች ደግሞ ሁሌም ስለማይገኙ ዘላቂነታቸው ውሱን ሆኖ ቆይቷል፡፡

ይህ ጥናት ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል አዲስ ስልት አስተዋውቋል፡፡ ይህም የክብካቤ ማበረታቻውን ከማይቀረው የመሬት ግብር ሥርዓት ጋር በማቆራኘት ዘላቂነት እንዲኖረው ማስቻል ነው፡፡ ስልቱ ታታሪ ገበሬዎችን የግብር ቅነሳ እንዲኖራቸው የሚጠይቅ ሲሆን መሬት የማይንከባከቡ ገበሬዎችን ደግሞ የግብር ጭማሪ እንዲጣልባቸው የሚጠይቅ ነው፡፡

ሥልቱ በገበሬው ቀጥተኛ ተሳትፎ፤ በአነስተኛ የሙያና የእውቀት ግብአት ሊከናወን የሚችል በመሆኑ አሰራሩንና ተቀባይነቱን ቀላል ያደርገዋል፡፡ በሂደትም የገበሬውን የመሬት ክብካቤ ባህል እያጠናከረ የመሬቱንም የመጎሳቆል ችግር እየቀረፈ፤ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥም የራሱን አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡ ለእንቅስቃሴው የሚያስፈልገው ወጪም ከመሬት ግብር ከሚሰበሰበው (በ1992 ዓ.ም ስሌት) የመንግስት አመታዊ ገቢ 1.1% ብቻ በመሆኑ በሀገሪቱ አቅም ብቻ እንኳ ብዙ ለውጥ ማምጣት ያስችላል ተብሎ ይገመታል፡፡

አዲሱ ስልት የሚሰጠውን ጠቀሜታ እና ተያያዥ ጉዳዮችን የበለጠ ለመመርመር እንዲያስችል የጉዳዩ ባለቤቶች የሆኑት ገበሬዎች፤ የግብርናና የልማት ባለሙያዎች፤ የሲቪል ማኅበራት፤ በተለያየ እርከን ደረጃ የሚገኙ የፖለቲካ አመራሮች በሰፊው ተወያይተውበት ሊያሻሽሉትና ሊያዳብሩት ይገባል፡፡

ዳንኤል ካሳሁን (ዶ/ር)
የማኅበራዊ ጥናት መድረክ ተመራማሪ

**ምንጭ፡-** Daniel Kassahun. Towards the Development of Differential Land Taxation System in Ethiopia. Paper presented at the Conference on Land and the Challenge of Sustainable Development in Ethiopia, August 2005, Addis Ababa.

**Address: Forum for Social Studies ♦ P. O. Box 25864 code 1000 ♦ Addis Ababa, Ethiopia**
**Telephone: (251-11)157 2990/91 ♦ Fax: (251-11) 157 2979**
**E-mail: fss@ethionet.et ♦ Home page: www.fssethiopia.org.et**